አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

**OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA**

ዘጠነኛ አመት ቁጥር ፶
አዲስ አበባ ሀምሌ ፪ ሺ፱ ዓ.ም

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

**Nine year No. 50**
**ADDIS ABEBA July 2017**


**<u>ማውጫ</u>**


**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የ፪ሺ፲ በጀት ዓመት የበጀት አዋጅ ቁጥር ፶/፪ሺ፱**


**<u>CONTENTS</u>**


Proclamation No. 50 /2017
Addis Abeba City Government 2010.C Fiscal Year Budget proclamation


አዋጅ ቁጥር ፶/፪ሺ፱

## <u>የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የበጀት አዋጅ</u>

ለ፪ሺ፲ ዓ.ም የበጀት ዓመትበአዲስ አበባ ከተማ ለሚከናወኑ ሥራዎችና አገልግሎቶች የሚያስፈልገውን በጀት አጽድቆ በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ወቅት ሥራ ላይ ማዋል አስፈላጊ በመሆኑ፣

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፲፬(፩) (ለ) መሠረት ይህን አዋጅ አውጥቷል።

## <u>ክፍል አንድ</u>
## <u>ጠቅላላ</u>

### ፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የ፪ሺ፲ በጀት ዓመት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የበጀት አዋጅ ቁ. ፶/፪ሺ፱ ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

Proclamation No 50/2017

## <u>BUDGET PROCLAMATION OF ADDIS ABEBA CITY ADMINISTRATION</u>

WHERE AS, it has become necessary to approve and disburse on time the budgetary appropriation for under taking by the Addis Ababa City Government during the 2010 (E.C) fiscal year.

NOW THEREFORE, in accordance with Article 14(1) (B) of the Addis Ababa City Government Revised charter proclamation No 361/2003 the Council of Addis Ababa City Government proclaimed as follow;

## <u>PART ONE</u>
## <u>GENERAL</u>

### 1. <u>Short Title</u>

This proclamation may be cited as the "Addis Abeba City Government 2010 fiscal year Budget Proclamation No 50/2017"


ያንዱ ዋጋ
Unit Price

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ፳፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

## ፪. የተፈቀደ በጀት

ከሐምሌ ፩ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ ፴ ቀን ፪ሺ፲ በሚፈፀመው በአንድ የበጀት ዓመት ጊዜ ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከሚገኘው ገቢ እና ከሌላ ገንዘብ ላይ ከዚህ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ ውስጥ ለተጠቀሱት ሥራዎችና አገልግሎቶች ቀጥሎ እንደተመለከተው፣

**ሀ/ ለማዕከል መ/ቤቶች**

| | |
|---|---|
| ፩.ለመደበኛ ወጪ.ዎች ብር | 7,137,594,002.00 |
| ፪. ለካፒታል ወጪ.ዎችብር | 19,135,730,196.00 |
| ፫. ለመጠባበቂያ በጀትብር | 3,200,000,000.00 |
| **ድምር** | 29,473,324,218.00 |

**ለ /ለክፍለ ከተሞች**

| | |
|---|---|
| ፩.ለመደበኛ ወጪ.ዎች ብር | 8,626,420,734.00 |
| ፪. ለካፒታል ወጪ.ዎች ብር | 2,400,537,708.00 |
| **ድምር** | 11,026,958,442.00 |
| **ጠቅላላ ድምር ብር** | 40,500,282,660.00 |

ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጪ ሆኖ እንዲከፈል በዚህ አዋጅ ተፈቅዷል።

## ክፍል ሁለት
## የበጀት አስተዳደር

### ፫. የከተማ አስተዳደር አካላት ሥልጣን

**፩.** የክፍለ ከተማ የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ኃላፊ ለክፍለ ከተማው ሥራና አገልግሎት በዚህ አዋጅ የተፈቀደለትን በጀት በሚጠይቅበት ጊዜ የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ኃላፊ ከከተማው አስተዳደር ገቢና ከሌላ ምንጭ እንዲከፍል ተፈቅዶለት ታዟል።

፪. ጉዳዩ የሚመለከታቸው መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ለየመስሪያ ቤቶቻቸው ሥራና አገልግሎት በዚህ አዋጅ የተፈቀደላቸውን በጀት በሚጠይቁበት ጊዜ እንደአግባብነቱ የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ኃላፊ ወይም የክፍለ ከተማው ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ከከተማው አስተዳደር ገቢና ከሌላ ምንጭ ወይም ለክፍለከከተማው አስተዳደር ገቢና ከሌላ ምንጭ ወይም ለክፍለ ከተማው ከተፈቀደው በጀት እንዲከፍል ተፈቅዶለት ታዟል፡፡



## 2. Allocated Budget

The Addis Abeba City Administration Budget is here by appropriated for the fiscal year commencing on July 1,2009 E.C. and ending on June 30, 2010 E.C. from Addis Ababa City Administration revenues and other funds, for the purposes and services set forth in the schedule here to;

**A/ City Sector Bureaus**

| | |
|---|---|
| 1. for Recurrent Expenditure Birr | 7,137,594,002.00 |
| 2. for Capital Expenditure Birr | 19,135,730,196.00 |
| 3. for Contingency Birr | 3,200,000,000.00 |
| **Total** | 29,473,324,218.00 |

**B/ Sub Cities**

| | |
|---|---|
| 1. Recurrent Expenditure Birr | 8,626,420,734.00 |
| 2. Capital Expenditure Birr | 2,400,537,708.00 |
| **Total** | 11,026,958,442.00 |
| **Grand Total Birr** | 40,500,282,660.00 |

## PART TWO
## BUDGET ADMINSTRATION

### 3. POWER OF THE CITY GOVERNMENT ORGANS

1. The head of Finance and Economic Development Bureau is here by authorized and directed up on the Request of the head of the Finance and Economic Development Office of a sub-city to disburse out of the City Government revenues and other funds the amounts appropriated here in for the purposes and services off a sub-city.
2. The head of Finance and Economic Development Bureau, or head of Finance and Economic Development Office of a sub-city is here by authorized upon the request of the heads of the concerned public bodies, to disburse out of the city Governments revenues and other funds or out of a sub-city's appropriate budget the amount appropriated here in for the purposes and services of this respective bodies.

፫. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥር የሚተዳደሩት ሆስፒታሎች፣ጤና ጣቢያዎች፣ ትምህርት ቤቶች፤ የቴክኒክና ሙያ ት/ት ተቋማትና ኮሌጆች፣ የኮተቤ ሜትሮፖሊታያን ዩንቨርስቲ፣ የአዲስ አበባ ውኃና ፍሳሽ ባለሥልጣን፣ የቲያትር ቤቶች፣ የሙያ ብቃትና ምዘና ማረጋገጫ ማዕከል፣የጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደላቸውን ጠቅላላ የበጀት መጠን ሳያልፍ ከዘመኑ በጀት ዓመት ገቢያቸው እንደአስፈላጊነቱ ወጪ እያደረጉ ቀጥታ በጥቅም ላይ በማዋል እና ይህንኑ ሂሣብ በመሥሪያ ቤቱ ኘሮግራም፣ የሥራ ክፍል፣ የሂሣብ መደብ መዝግበው በመያዝ በየወሩ ለፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ማሳወቅ አለባቸው።

፬. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በዚህ አዋጅ ላይ ላልተመለከቱ ለካፒታልም ሆነ ለመደበኛ ተጨማሪ ሥራዎች ከውጭ ብድር እንዲሁም ከአገር ውስጥም ሆነ ከውጪ ሀገር በዓይነት ወይም በጥሬ ገንዘብ የሚያገኙትን ብድር ወይም እርዳታ በሥራ ላይ በማዋል እና ይህንኑ ሂሣብ በመሥሪያ ቤቱ አርእስት፣ በንዑስ አርዕስት ኘሮግራም፣ በኘሮጀክት ሥር መዝግበውበተጨማሪ በጀት በመያዝ የበጀት ዓመቱ ከመጠናቀቁ በፊት ለፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ሪፖርት ማድረግ አለባቸው።

## ፬.<u>የበጀት ዝውውር</u>

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ፩፮/፪ሺ፪ አንቀጽ ፳፪ እና ፳፯ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፡ የበጀት ዝውውር በሚከተለው ሁኔታ ይፈፀማል፤

፩. በመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ የሚደረግ የበጀት ዝውውር

፩. የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ኃላፊዉ:-

ሀ/በመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ መደበኛ በጀትን በሚመለከቱ የወጪ መደቦች ውስጥ የበጀት ዝውውር ለማድረግ፣

ለ/ በአንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ በጀትን ከአንድ ካፒታል ኘሮጀክት ወደ ሌላ የካፒታል ኘሮጀክት ለማዘዋወር፣



3. Hospitals, Health Centers, Water & Sewerage Authority, Schools, Theater houses, TVET Colleges, Kotobe Metropolitan University, Professional competency and evaluation Center, Gulele Botanic Garden are allowed to retain and expend within the limit of their budgetary appropriations receipts from the current fiscal year and shall record the amount under its program, department, and codes and shall report monthly to Finance and Economic Development Bureau.

. 4. Public bodies are hereby authorized to record on their appropriate budgetary head, sub head, project, or program, as the case may be, and undertake all acts necessary for the Utilization of any additional loan or aid in kind and/or cash obtained from foreign or local source for carrying out capital project or recurrent programs, and report to the Finance and Economic Development Bureau before the end of the budget year.

## 4. <u>BUDGET TRANSFER</u>

Without prejudice to the provisions of Article 22 and 27 of the Addis Ababa City Government Financial Administration proclamation No16/2010 budget transfer shall be executed as follows:

### 1) **Budget Transfers within Public Bodies**

1) The Finance & Economic Development Bureau Head may within a Public Body:

(a) transfer funds within items of expenditure of the recurrent Budget;

(b) transfer budget from one capital project to another within a Public Body ;

ሐ/አስቀድሞ ባሉት ዓመታት ለተፈቀደ እና በበጀት ዓመቱ በጀት ላልተያዘለት የካፒታል ፕሮጀክት ቀሪ ግዴታዎች ማስፈፀሚያ የሚውል በጀት ለአስፈፃሚ መሥሪያ ቤቱ ከተፈቀደ የካፒታል በጀት ለማዘዋወር፣

መ/በአንድ የመንግሥት መ/ቤት ሥር ያሉ መ/ቤቶች ሲዋሀዱ ወይም ሲነጣጠሉ በጀቱን ከአንዱ ወደሌላው ለማዘዋወር፣ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

፪. የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማትየቢሮ ኃላፊዉ ፡ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተሰጠውን ሥልጣን በውክልና አግባብ ላለው የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፪. በከተማውማዕከል እና በክፍለ ከተማዎች ወይም በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች መካከል የሚደረግ የበጀት ዝውውር

፩ አንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የተፈቀደለትን የመደበኛ በጀት የማይጠቀምበት ሆኖ ሲገኝ የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ኃላፊዉ በጀቱን ወደሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ለማዘዋወር ይችላል፡፡

፪ የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ኃላፊዉ በሚከተሉት ምክንያቶች የአንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የካፒታል በጀት ወደ ሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የካፒታል በጀት እንዲዘዋወር ሊፈቅድ ይችላል፡-

ሀ. በአንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ ያጋጠመውን የካፒታል በጀት እጥረት ለማቃለል በበጀት ዓመቱ ለሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የተፈቀደ እና ጥቅም ላይ ያልዋለን የካፒታል በጀት በማዘዋወር መጠቀም አስፈላጊ ሲሆንና ይህም ተጨማሪ በጀት ያስፈለገው ቀደም ሲል ለተፈቀደ የካፒታል ፕሮጀክት መሆኑ ሲረጋገጥ፣

(c) Transfer the budget approved for capital expenditure of the Public Body to finance pending obligations of a project approved in previous years for which no budget is allocated in the current fiscal year;

(d) Transfer the budget when organs under a Public Body merge or split.

2) The Finance & Economic Development Bureau Head may delegate the appropriate head of public body to exercise the power vested in him under sub- article 1 of this Article

2) **Budget Transfers between Public Bodies& Sub cities**

1. The Finance & Economic Development Bureau Head may transfer a recurrent budget from one Public Body to the other if it is ascertained that the Public Body to which the budget is appropriated cannot wholly utilize its budget,

2. The Finance & Economic Development Bureau Head may authorize the transfer of funds from the capital budget of one Public Body to the capital budget of another Public Body under the following conditions:

(a) Where a deficiency in one Public Body's capital budget can be met by an offsetting transfer from another Public Body's capital budget approved for that fiscal year provided the capital budget receiving additional funds is a previously approved capital budget.

ለ. አስቀድሞ ባሉት ዓመታት ለተፈቀደ እና በበጀት ዓመቱ በጀት ላልተያዘለት ፕሮጀክት ቀሪ ግዴታዎች ማስፈፀሚያ የሚውል በጀት ጥያቄ የቀረበ እንደሆነ፡፡

(b) Where a budget is requested to finance pending obligations of a project approved in previous years for which no budget is allocated in the current fiscal year.

## ፫. ከማዕከል ወደ ክፍለ ከተማ የሚደረግ የበጀት ዝውውር

የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ኃላፊዉ ተራፊ በጀት መኖሩን ሲያረጋግጥ ከማዕከል ወደ ክፍለ ከተማው ወይም ከክፍለ ከተማ ወደ ማዕከል በጀት ሊያዛውር ይችላል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የክፍለ ከተማ ጽ/ቤት ኃላፊ የክፍለ ከተማ የሴክተር መ/ቤት ኃላፊዎች በሚያቀርቡት ጥያቄ መሠረት ከክፍለ ከተማ ወደ ማዕከል በጀት ሊያዛውር ይችላል፡፡

## 3) Budget Transfers in-between Public Bodies and Sub cities

The Finance & Economic Development Bureau Head, on the conformation of any unused budget, may transfer a budget from a center Public Body to the sub city or from Sub City to Center public body. With the same manner the sub city Finance and Economic Development Office Head may transfer budgets from a sub city to a center Public Body.

## ፭. በጀት ዝውውር መደረጉን ስለማሳወቅ

በዚህ አዋጅ በጀትን የማዛወር ሥልጣን የተሰጣቸው አካላትና ኃላፊዎች የበጀት ዝውውሩን እንደፈቀዱ ወዲያውኑ እንደአግባብነታቸው ለቢሮው ወይም ለጽሕፈት ቤቱ በጽሁፍ ማሳወቅ አለባቸው።

## 5 .NOTIFICATION OF BUDGET TRANSFER

According to this proclamation, the authorized officials and heads of public bodies for transferring budget shall immediately notify in writing to the Finance and Economic Development Bureau or Office as the case may be.

አዲስ አበባ
ሐምሌ 6 ቀን 2009

Done at Addis Ababa
July,13 2017

ድሪባ ኩማ
የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ

Dirba Kuma
Mayor of Addis Ababa City

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የ2010 በጀት ዓመት የገቢና የወጪ አሸፋፈን

### 1. ገቢ

| | |
|---|---|
| **የከተማው ገቢ** | **ብር** |
| **ሀ. የአገር ውስጥ ገቢ** | |
| ታክስ ገቢ | 30,597,102,016.31 |
| ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች | 3,528,055,478.10 |
| የማዘጋጃ ቤት ነክ አገልግሎቶች ገቢ | 4,380,864,016.59 |
| የመንገድ ፈንድ | 67,431,922.00 |
| የአገር ውስጥ ገቢ ድምር | **38,573,453,433.00** |
| **ለ. የውጭ እርዳታና ብድር** | |
| የውጭ ዕርዳታ | 42,792,902.00 |
| የውጭ ብድር | 1,884,036,325.00 |
| የውጭ እርዳታና ብድርድምር | **1,926,829,227.00** |
| **የከተማው ጠቅላላ ገቢ ድምር** | **40,500,282,660.00** |

### 2.ወጪ

| | |
|---|---|
| **ሀ. መደበኛ ወጪ** | **ብር** |
| የመደበኛ ወጪ ድምር | 15,764,014,756.00 |
| **ለ. የካፒታል ወጪ** | |
| የካፒታል ወጪ ድምር | 21,536,267,904.00 |
| **ሐ. የመጠባበቂያ ወጪ** | |
| የመጠባበበቂያ ድምር | 3,200,000,000.00 |
| **ጠቅላላ የወጪ ድምር** | **40,500,282,660.00** |

## 1. ለክፍለ ከተሞች የተመደበ በጀት

| | መደበኛ ወጪ | ካፒታል ወጪ | |
|---|---|---|---|
| **ጠቅላላ ድምር** | | | |
| **የክፍለ ከተሞች ጠቅላላ ድምር** | **8,626,420.734** | **2,400,537.708** | **11,026,958.442** |
| አራዳ ክፍለ ከተማ | 724,643.904 | 231,806.262 | 956,450.166 |
| አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ | 717,320.970 | 150,483.647 | 867,804.617 |
| ልደታ ክፍለ ከተማ | 679,914.960 | 140,703.690 | 820,618.650 |
| ቂርቆስ ክፍለ ከተማ | 758,915.868 | 249,195.126 | 1,008,110.994 |
| የካ ክፍለ ከተማ | 951,332.242 | 165,067.181 | 1,116,399.423 |
| ቦሌ ክፍለ ከተማ | 965,020.480 | 298,518.682 | 1,263,539.162 |
| አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ | 911,429.079 | 293,512.414 | 1,204,941.493 |
| ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ | 932,006.133 | 315,638.989 | 1,247,645.122 |
| ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ | 1,193,473.664 | 378,337.245 | 1,571,810.909 |
| ጉለሌ ክፍለ ከተማ | 792,363.434 | 177,274.472 | 969,637.906 |

## 4. ለክፍለ ከተሞች የተመደበ በጀት በፋይናንስ ምንጭ

| ክፍለ ከተማ | ከመንግስት ግ/ቤት | ከውስጥ ገቢ | ድምር |
|---|---|---|---|
| አራዳ ክፍለ ከተማ | 930,407.166 | 26,043.000 | 956,450.166 |
| አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ | 855,074.806 | 12,729.811 | 867,804.617 |
| ልደታ ክፍለ ከተማ | 807,590.707 | 13,027.943 | 820,618.650 |
| ቂርቆስ ክፍለ ከተማ | 986,254.630 | 21,856.364 | 1,008,110.994 |
| የካ ክፍለ ከተማ | 1,098,199.383 | 18,200.040 | 1,116,399.423 |
| ቦሌ ክፍለ ከተማ | 1,238,447.312 | 25,091.850 | 1,263,539.162 |
| አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ | 1,187,414.274 | 17,527.219 | 1,204,941.493 |
| ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ | 1,223,379.442 | 24,265.680 | 1,247,645.122 |
| ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ | 1,528,023.528 | 43,787.381 | 1,571,810.909 |
| ጉለሌ ክፍለ ከተማ | 952,658.906 | 16,999.000 | 969,637.906 |
| **ድምር** | 10,807,450.154 | 219,528.288 | 11,026,958.442 |

# ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION 2008 ETHIOPIAN FISCAL YEAR BUDGET

## EXPENDITURE COVERAGE

## 1. REVENUE

| City Administration Revenue Birr | Total Birr | |
|---|---|---|
| A. Domestic Revenue | | |
| Tax revenue | 30,597,102, 016.31 | |
| Non-tax revenue | 3,528,055,478.10 | |
| Municipal service revenue | 4,380,864,016.59 | |
| Road funds | 67,431,922.00 | |
| **Domestic Revenue Total** | | **38,573,453,433.00** |
| B. External Assistance and Loan | | |
| External Assistance | 42,792,902.00 | |
| External Loan | 1,884,036,325.00 | |
| **External Assistance and Loan Total** | **1,926,829,227.00** | |
| **Revenue Total** | | **40,500,282,660.00** |

## 2. EXPENDITURE

| | | |
|---|---|---|
| **A. Recurrent Expenditure** | | |
| **Recurrent Expenditure Total** | 15,764,014,756.00 | |
| **B. Capital Expenditure** | | |
| **Capital Expenditure Total** | 21,536,267,904.00 | |
| **C. Contingency** | | |
| **Contingency Total** | 3,200,000,000.00 | |
| **Total Expenditure** | | **40,500,282,660.00** |

## 3. Budget for Sub-Cities

| | Recurrent Expenditure | Capital Expenditure | Total |
|---|---|---|---|
| **Sub-Cities** Total | **8,626,420.738** | **2,400,537.708** | **11,026,958.446** |
| Arada | 724,643.904 | 231,806.262 | 956,450.166 |
| Addis Ketema | 717,320.970 | 150,703.690 | 867,804.617 |
| Lideta | 679,914.960 | 140,703.690 | 820,618.650 |
| Kirkos | 758,915.868 | 249,195.126 | 1,008,110.994 |
| Yeka | 951,332.245 | 165,067.181 | 1,116,399.426 |
| Bole | 965,020.480 | 298,518.682 | 1,263,539.162 |
| Akaki Kaliti | 911,429.079 | 293,512.414 | 1,204,941.439 |
| Nefas Silk Lafto | 932,006.134 | 315,638.989 | 1,247,645.122 |
| Kolfe Keranio | 1,193,473.664 | 378,337.245 | 1,571,810.909 |
| Gulele | 792,363.434 | 177,274.472 | 969,637.906 |

## 4. Sub-Cities Budget by Source of Finance

| Sub-Cities | Treasury | Retained Revenue | Total |
|---|---|---|---|
| Arada | 930,407.166 | 26,043.000 | 956,450.166 |
| Addis Ketema | 855,074.806 | 12,729.811 | 867,804.617 |
| Lideta | 807,590.707 | 13,027.943 | 820,618.650 |
| Kirkos | 986,254.630 | 21,856.364 | 1,008,110.994 |
| Yeka | 1,098,199.383 | 18,200.040 | 1,116,399.423 |
| Bole | 1,238,447.312 | 25,091.850 | 1,263,539.162 |
| Akaki Kaliti | 1,187,414.274 | 17,527.219 | 1,204,941.493 |
| Nefas Silk Lafto | 1,223,379.442 | 24,265.680 | 1,247,645.122 |
| Kolfe Keranio | 1,528,023.528 | 43,787.381 | 1,571,810.909 |
| Gulele | 952,658.906 | 16,999.000 | 969,637.906 |
| | 10,807,450.154 | 219,528.288 | 11,026,958.446 |